የጌታችንን አምላክነት የሚያሳዩ ጥቅሶች (ለሙስሊም አድማጭ)

ሙስሊሞች ጋር ስለጌታችን አምላክነት ስትወያዩ እንደክርስቲያን መወያየት አይገባችሁም። ከክርስቲያኖች ጋር ስትወያዩ መጽሐፍ ቅዱስን ከዐውዱ፣ ከሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍላት ጋር፣ ወዘተረፈ. . . እያጣቀሳችሁ እየመረመራችሁ ነው የጌታችንን አምላክነት የምታሳዩት። ይህንን መንገድ ለሙስሊሞች መጠቀም ትችላላችሁ ፥ ነገር ግን ቀጥታ ልባቸው ላይ ይህንን መንገድ ተጠቅማችሁ አትገቡም። እውነት የሙስሊምን ልብ መምታት ከፈለጋችሁ የራሱ መንገድ አለው። ታዲያ ይህ መንገድ ምንድን ነው??? በዋነኝነት ትኩረታችሁ የሚሆነው ቁርአንና መጽሐፍ ቅዱስን አብራችሁ መጠቀም ይሆናል። በቁርአን ውስጥ ለአምላክ ብቻ የተነገሩ ንግግሮች አሉ። እኒህን ራሳቸውን ንግግሮች ግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ለጌታችን ለክብር ባለቤት ለኢየሱስ ክርስቶስ ሲጠቀመው እንመለከታለን። በዚህ መንገድ ነው ሙስሊሞችን በደንብ እንዲያስቡበት የምታደርጉት ፥ ስለዚህ በእኒህ መንገዶች ለሙሲሎሞች እንዴት የጌታችንን አምላክነት የምታሳዩት እንቀጥል። አምላካችን ሆይ ርዳን፣ አምላካችን ሆይ ሙስሊሞችን ማርከህ አምጣቸው፣ መሐመድን በሲያል ውስጥ እንደወቃኸው አቤቱ ከልባቸው ይህንን ሰውዬ ወቅተህ አውጣው ፥ አሁንም ጎዩል ጠበቃ ሁንን። አሜን።

በመጀመሪያ በእስልምና ያለውን ስለ አላህ ያለ አስተምህሮ መካከል አንዱን ለእኛ የሚጠቅመንን ነቅሠን እናወጣለን። ይህ አስተምህሮ የአላህን ስሞች የሚመለከት ነው። በዋነኝነት በሱኒ ሙስሊም አስተምህሮ ውስጥ ከአላህ በቀር ለሌላ ለማንም የማይሰጡ ስሞች አሉ። እኒህ ስሞች የአላህ ልዩ ስሞቹ ናቸው ፥ እኒህ ስሞችን ከአላህ ውጪ ለሌላ አካል መስጠት ማለት ሺርክ ነው። ምክንያቱም እኒህን ስሞች ለሌላ አካል መስጠት ማለት ያንን አካል ከአላህ እኮል ማድረግ በመሆኑ። እኒህን ስሞች ስንመለከት ግን መጠንቀቅ ያለብን ነገር አለ። እንደምሳሌ አንዱን ስም ወስጀ እንደምሳሌ ልጠቀመው፥

ከአላህ ስሞች መካከል አንዱ 'አል-ራሕማን' (ርኅሩኑ) ነው። 'አል-' የሚለው ቃል በዐማርኛ በትክክል የሚመስለው ቃል ማግኘት ያስቸግራል። ይልቁንም በኢንግሊዘኛው 'The' የግሪኩን ደግሞ 'O' የሚለውን ቃል የሚተካ ነው። ከአላህ ውጪ ሌላ ሰው 'ራሕማን' ሊባል ይችላል ፥ ነገር ግን ከአላህ ውጪ መቼም ቢሆን ማንም 'አል-ራሕማን' ተብሎ ሊጠራ አይችልም። 'The Merciful' ተብሎ ማንም ሊጠራ አይችልም እንደማለት ነው በእስልምና አስተምህሮ ፥ 'Merciful' ተብሎ አንድ ሰው ሊጠራ ይችላል። ነገር ግን 'The Merciful' (ያ የሚራራው) ተብሎ ሊጠራ አይችልም። ይህንን ነጥብ በደንብ ከያዝን እንቀጥል።

እንደእስልምና አስተምህሮ አላህ 99 ስሞች አሉት። ይህንን በተለያዩ ሐዲሦች ውስጥ እንመለከታለን። የተወሰኑ ምሳሌዎችን ልስጥ፥

/Jami' At-Tirmidhi/ (ጃሚ አትቲርሚዲ)

حَدَّثَنَا ابْنُ أَبِي عُمَرَ، حَدَّثَنَا سُفْيَانُ بْنُ عُيَيْنَةَ، عَنْ أَبِي الزِّنَادِ، عَنِ الأَعْرَجِ، عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ، عَنِ النَّبِيِّ صلى الله عليه وسلم قَالَ " إِنَّ لِلَّهِ تِسْعَةً وَتِسْعِينَ اسْمًا مَنْ أَحْصَاهَا دَخَلَ الْجَنَّةَ " . قَالَ وَلَيْسَ فِي هَذَا الْحَدِيثِ ذِكْرُ الأَسْمَاءِ . قَالَ وَهَذَا حَدِيثٌ حَسَنٌ صَحِيحٌ . رَوَاهُ أَبُو الْيَمَانِ عَنْ شُعَيْبِ بْنِ أَبِي حَمْزَةَ عَنْ أَبِي الزِّنَادِ وَلَمْ يَذْكُرْ فِيهِ الأَسْمَاءَ .

Abu Hurairah narrated that the Prophet said: "Indeed, Allah has ninety-nine Names, whoever counts them shall enter Paradise."

አቡ ሁረይራ እንዳስተላለፉት ነብዩ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- "አላህ ዘጠና ዘጠኝ ስሞች አሉት፣ የቀጠራቸውም ሰው ጀነት ይገባል።

Jami` at-Tirmidhi 3508

Grade: Sahih (Darussalam)

https://sunnah.com/tirmidhi:3508

/Sunan Ibn Majah/ (**ሱናን ኢብን ማጃህ**)

حَدَّثَنَا أَبُو بَكْرِ بْنُ أَبِي شَيْبَةَ، حَدَّثَنَا عَبْدَةُ بْنُ سُلَيْمَانَ، عَنْ مُحَمَّدِ بْنِ عَمْرٍو، عَنْ أَبِي سَلَمَةَ، عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ، قَالَ قَالَ رَسُولُ اللَّهِ ـ صلى الله عليه وسلم ـ " إِنَّ لِلَّهِ تِسْعَةً وَتِسْعِينَ اسْمًا مِائَةً إِلاَّ وَاحِدًا مَنْ أَحْصَاهَا دَخَلَ الْجَنَّةَ " .

It was narrated from Abu Hurairah that: the Messenger of Allah (saas) said: "Allah has ninety-nine Names, one hundred less one. Whoever counts them will enter Paradise."

ከአቡ ሁረይራህ (ረዲየላሁ ወንሁ) እንደተረከው፣ የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- "አላህ ዘጠና ዘጠኝ ስሞች አሉት፣ ከመቶ በአንድ ያነሱ ስሞች አሉት። የቀጠራቸው ጀነት ይገባል።

Sunan Ibn Majah 3860

Grade: Hasan (Darussalam)

https://sunnah.com/ibnmajah:3860

/Jami' At-Tirmidhi/ (**ጃሚ አትቲርሚዲ**)

حَدَّثَنَا يُوسُفُ بْنُ حَمَّادٍ الْبَصْرِيُّ، حَدَّثَنَا عَبْدُ الأَعْلَى، عَنْ سَعِيدٍ، عَنْ قَتَادَةَ، عَنْ أَبِي رَافِعٍ، عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ، رَضِيَ اللَّهُ عَنْهُ عَنِ النَّبِيِّ صلى الله عليه وسلم قَالَ " إِنَّ لِلَّهِ تِسْعَةً وَتِسْعِينَ اسْمًا مِائَةً غَيْرَ وَاحِدٍ مَنْ أَحْصَاهَا دَخَلَ الْجَنَّةَ " .

قَالَ يُوسُفُ وَحَدَّثَنَا عَبْدُ الأَعْلَى، عَنْ هِشَامِ بْنِ حَسَّانَ، عَنْ مُحَمَّدٍ، عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ، رضى الله عنه عَنِ النَّبِيِّ صلى الله عليه وسلم هَذَا حَدِيثٌ حَسَنٌ صَحِيحٌ . وَقَدْ رُوِيَ مِنْ غَيْرِ وَجْهٍ عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ عَنِ النَّبِيِّ صلى الله عليه وسلم . .

Abu Hurairah [may Allah be pleased with him] narrated the the Prophet said: "Indeed Allah has ninety-nine Names, one hundred less one, whoever counts them shall enter Paradise."

አቡ ሁረይራ (ረዲየላሁ ወንሁማ) እንዳስተላለፉት ነብዩ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- "በእርግጥ አላህ ዘጠና ዘጠኝ ስሞች አሉት፣ ከመቶ በአንድ ያነሰ፣ የቆጠራቸውም ጀነት ይገባቸዋል።

Jami` at-Tirmidhi 3506

Grade: Hasan (Darussalam)

https://sunnah.com/tirmidhi:3506

/Sahih al-Bukhari/ (ሳሒሕ አል-ቡሃሪ)

حَدَّثَنَا عَلِيُّ بْنُ عَبْدِ اللَّهِ، حَدَّثَنَا سُفْيَانُ، قَالَ حَفِظْنَاهُ مِنْ أَبِي الزِّنَادِ عَنِ الأَعْرَجِ، عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ، روَايَةً قَالَ " لِلَّهِ تِسْعَةٌ وَتِسْعُونَ اسْمًا، مِائَةٌ إِلاَّ وَاحِدًا، لاَ يَحْفَظُهَا أَحَدٌ إِلاَّ دَخَلَ الْجَنَّةَ، وَهْوَ وَتْرٌ يُحِبُّ الْوَتْرَ ".

Narrated Abu Huraira: Allah has ninety-nine Names, i.e., one hundred minus one, and whoever believes in their meanings and acts accordingly, will enter Paradise; and Allah is witr (one) and loves 'the witr' (i.e., odd numbers).

አቡ ሁረይራ እንደተረከው፡- አላህ ዘጠና ዘጠኝ ስሞች አሉት፣ ማለትም ከመቶ በአንድ ሲቀነስ፣ በትርጉማቸው አምኖ የሰራ ሰው ጀነት ይገባል። እና አላህ ዊትር (አንድ) ነው እና 'ዊትር'ን ይወዳል (ማለትም፣ የማይከፈሉ ቁጥሮችን)።

Sahih al-Bukhari 6410

https://sunnah.com/bukhari:6410

/Sahih al-Bukhari/ (ሳሒሕ አል-ቡሃሪ)

حَدَّثَنَا أَبُو الْيَمَانِ، أَخْبَرَنَا شُعَيْبٌ، حَدَّثَنَا أَبُو الزِّنَادِ، عَنِ الأَعْرَجِ، عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ ـ رضى الله عنه ـ أَنَّ رَسُولَ اللَّهِ صلى الله عليه وسلم قَالَ " إِنَّ لِلَّهِ تِسْعَةً وَتِسْعِينَ اسْمًا مِائَةً إِلاَّ وَاحِدًا مَنْ أَحْصَاهَا دَخَلَ الْجَنَّةَ ".

Narrated Abu Huraira: Allah's Messenger (ﷺ) said, "Allah has ninety-nine names, i.e. one-hundred minus one, and whoever knows them will go to Paradise." (Please see Hadith No. 419 Vol. 8)

አቡ ሁረይራ እንደተረከው፣ የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ወ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- "አላህ ዘጠና ዘጠኝ ስሞች አሉት፣ ማለትም አንድ ከመቶ ሲቀነስ፣ የሚያውቃቸውም ጀነት ይገባል። (ሀዲስ ቁጥር 419 ቅጽ 8 ተመልከት)

Sahih al-Bukhari 2736

https://sunnah.com/bukhari:2736

/Sahih al-Bukhari/ (**ሳሒሕ አል-ቡሃሪ**)

حَدَّثَنَا أَبُو الْيَمَانِ، أَخْبَرَنَا شُعَيْبٌ، حَدَّثَنَا أَبُو الزِّنَادِ، عَنِ الأَعْرَجِ، عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ، أَنَّ رَسُولَ اللَّهِ صلى الله عليه وسلم قَالَ " إِنَّ لِلَّهِ تِسْعَةً وَتِسْعِينَ اسْمًا مِائَةً إِلاَّ وَاحِدًا، مَنْ أَحْصَاهَا دَخَلَ الْجَنَّةَ ". {أَحْصَيْنَاهُ} حَفِظْنَاهُ.

Narrated Abu Huraira: Allah's Messenger (ﷺ) said, "Allah has ninety-nine Names, one-hundred less one; and he who memorized them all by heart will enter Paradise." To count something means to know it by heart.

አቡ ሁረይራ እንደተረከው፣ የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ወ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- "አላህ ዘጠና ዘጠኝ ስሞች አሉት፣ ከመቶ በአንድ ያነሱ ስሞች አሉት። ሁሉንም በቃላቸው የሸመደው ጀነት ይገባል። አንድን ነገር መቁጠር ማለት በልብ ማወቅ ማለት ነው።

Sahih al-Bukhari 7392

https://sunnah.com/bukhari:7392

/Sahih Muslim/ (**ሳሒሕ ሙስሊም**)

حَدَّثَنِي مُحَمَّدُ بْنُ رَافِعٍ، حَدَّثَنَا عَبْدُ الرَّزَّاقِ، حَدَّثَنَا مَعْمَرٌ، عَنْ أَيُّوبَ، عَنِ ابْنِ سِيرِينَ، عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ، وَعَنْ هَمَّامِ بْنِ مُنَبِّهٍ، عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ، عَنِ النَّبِيِّ صلى الله عليه وسلم قَالَ " إِنَّ لِلَّهِ تِسْعَةً وَتِسْعِينَ اسْمًا مِائَةً إِلاَّ وَاحِدًا مَنْ أَحْصَاهَا دَخَلَ الْجَنَّةَ " . وَزَادَ هَمَّامٌ عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ عَنِ النَّبِيِّ صلى الله عليه وسلم " إِنَّهُ وِتْرٌ يُحِبُّ الْوِتْرَ " .

Abu Huraira reported Allah's Apostle (ﷺ) as saying: Verily, there are ninety-nine names for Allah, i. e. hundred excepting one. He who enumerates them would get into Paradise. And Hammam has made this addition on the authority of Abu Huraira who reported it from Allah's Apostle (ﷺ) that he said: " He is Odd (one) and loves odd number."

አቡ ሁረይራ እንደዘገቡት የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፦ "በእርግጥ የአላህ ስሞች ዘጠና ዘጠኝ ናቸው፣ ማለትም ከአንድ በቀር መቶ። የቆጠራቸው ጀነት ይገባ ነበር። ሐማምም ይህን ተጨማሪ ያደረገው አቡ ሁረይራ እንዳስተላለፉት ከአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) በዘገቡት መሰረት፦ "እርሱ ልዩ (አንድ) ነው እና ጎዶሎ (የማይካፈል) ቁጥርን ይወዳል።"

Sahih Muslim 2677b

https://sunnah.com/muslim:2677b

ስለዚህ በሐዲሥ ውስጥ ሙሉ ለሙሉ እንደምናረጋግጠው አላህ ዘጠና ዘጠኝ ስሞች አሉት። እኒህ ስሞች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፥ (https://99namesofallah.name/) በዚህ ሊንክ ገብታችሁ ሙሉ ዝርዝራቸውን መመልከት ትችላላችሁ። በዐማርኛ ደግሞ ለሚፈልግ (https://haddise.wordpress.com/99-%E1%8B%A8%E1%8A%A0%E1%88%8B%E1%88%85-%E1%88%B5%E1%88%9E%E1%89%BD%E1%8A%95-%E1%8A%A8%E1%8A%90%E1%89%B5%E1%88%AD%E1%8C%89%E1%88%9B%E1%89%B8%E1%8B%8D-%E1%8B%AB%E1%8B%8D%E1%89%83%E1%88%89/)

99 names of Allah – Meaning and Explanation

#	Name	Transliteration	Meaning
1	ٱلرَّحْمَـانُ	AR-RAHMAAN	The Most or Entirely Merciful
2	ٱلرَّحِيْمُ	AR-RAHEEM	The Bestower of Mercy
3	ٱلْمَلِكُ	AL-MALIK	The King and Owner of Dominion
4	ٱلْقُدُّوسُ	AL-QUDDUS	The Absolutely Pure
5	ٱلْسَّلَامُ	AS-SALAM	The Perfection and Giver of Peace
6	ٱلْمُؤْمِنُ	AL-MU'MIN	The One Who gives Emaan and Security
7	ٱلْمُهَيْمِنُ	AL-MUHAYMIN	The Guardian, The Witness, The Overseer
8	ٱلْعَزِيزُ	AL-AZEEZ	The All Mighty
9	ٱلْجَبَّارُ	AL-JABBAR	The Compeller, The Restorer
10	ٱلْمُتَكَبِّرُ	AL-MUTAKABBIR	The Supreme, The Majestic

11	ٱلْخَالِقُ	AL-KHAALIQ	The Creator, The Maker
12	ٱلْبَارِئُ	AL-BAARI’	The Originator
13	ٱلْمُصَوِّرُ	AL-MUSAWWIR	The Fashioner
14	ٱلْغَفَّارُ	AL-GHAFFAR	The All- and Oft-Forgiving
15	ٱلْقَهَّارُ	AL-QAHHAR	The Subduer, The Ever-Dominating
16	ٱلْوَهَّابُ	AL-WAHHAAB	The Giver of Gifts
17	ٱلرَّزَّاقُ	AR-RAZZAAQ	The Provider
18	ٱلْفَتَّاحُ	AL-FATTAAH	The Opener, The Judge
19	ٱلْعَلِيمُ	AL-‘ALEEM	The All-Knowing, The Omniscient
20	ٱلْقَابِضُ	AL-QAABID	The Withholder
21	ٱلْبَاسِطُ	AL-BAASIT	The Extender
22	ٱلْخَافِضُ	AL-KHAAFIDH	The Reducer, The Abaser
23	ٱلرَّافِعُ	AR-RAAFI’	The Exalter, The Elevator
24	ٱلْمُعِزُّ	AL-MU’IZZ	The Honourer, The Bestower
25	ٱلْمُذِلُّ	AL-MUZIL	The Dishonourer, The Humiliator
26	ٱلسَّمِيعُ	AS-SAMEE’	The All-Hearing
27	ٱلْبَصِيرُ	AL-BASEER	The All-Seeing
28	ٱلْحَكَمُ	AL-HAKAM	The Judge, The Giver of Justice
29	ٱلْعَدْلُ	AL-‘ADL	The Utterly Just
30	ٱللَّطِيفُ	AL-LATEEF	The Subtle One, The Most Gentle
31	ٱلْخَبِيرُ	AL-KHABEER	The Acquainted, the All-Aware
32	ٱلْحَلِيمُ	AL-HALEEM	The Most Forbearing

33	ٱلْعَظِيمُ	AL-‘ATHEEM	The Magnificent, The Supreme
34	ٱلْغَفُورُ	AL-GHAFOOR	The Forgiving, The Exceedingly Forgiving
35	ٱلشَّكُورُ	ASH-SHAKOOR	The Most Appreciative
36	ٱلْعَلِيُّ	AL-‘ALEE	The Most High, The Exalted
37	ٱلْكَبِيرُ	AL-KABEER	The Greatest, The Most Grand
38	ٱلْحَفِيظُ	AL-HAFEEDH	The Preserver, The All-Heedful and All-Protecting
39	ٱلْمُقِيتُ	AL-MUQEET	The Sustainer
40	ٱلْحَسِيبُ	AL-HASEEB	The Reckoner, The Sufficient
41	ٱلْجَلِيلُ	AL-JALEEL	The Majestic
42	ٱلْكَرِيمُ	AL-KAREEM	The Most Generous, The Most Esteemed
43	ٱلرَّقِيبُ	AR-RAQEEB	The Watchful
44	ٱلْمُجِيبُ	AL-MUJEEB	The Responsive One
45	ٱلْوَاسِعُ	AL-WAASI’	The All-Encompassing, the Boundless
46	ٱلْحَكِيمُ	AL-HAKEEM	The All-Wise
47	ٱلْوَدُودُ	AL-WADOOD	The Most Loving
48	ٱلْمَجِيدُ	AL-MAJEED	The Glorious, The Most Honorable
49	ٱلْبَاعِثُ	AL-BA’ITH	The Resurrector, The Raiser of the Dead
50	ٱلشَّهِيدُ	ASH-SHAHEED	The All- and Ever Witnessing
51	ٱلْحَقُّ	AL-HAQQ	The Absolute Truth
52	ٱلْوَكِيلُ	AL-WAKEEL	The Trustee, The Disposer of Affairs
53	ٱلْقَوِيُّ	AL-QAWIYY	The All-Strong
54	ٱلْمَتِينُ	AL-MATEEN	The Firm, The Steadfast

55	ٱلْوَلِيُّ	AL-WALIYY	The Protecting Associate
56	ٱلْحَمِيدُ	AL-HAMEED	The Praiseworthy
57	ٱلْمُحْصِيُ	AL-MUHSEE	The All-Enumerating, The Counter
58	ٱلْمُبْدِئُ	AL-MUBDI	The Originator, The Initiator
59	ٱلْمُعِيدُ	AL-MU'ID	The Restorer, The Reinstater
60	ٱلْمُحْيِى	AL-MUHYEE	The Giver of Life
61	ٱلْمُمِيتُ	AL-MUMEET	The Bringer of Death, the Destroyer
62	ٱلْحَىُّ	AL-HAYY	The Ever-Living
63	ٱلْقَيُّومُ	AL-QAYYOOM	The Sustainer, The Self-Subsisting
64	ٱلْوَاجِدُ	AL-WAAJID	The Perceiver
65	ٱلْمَاجِدُ	AL-MAAJID	The Illustrious, the Magnificent
66	ٱلْوَاحِدُ	AL-WAAHID	The One
67	ٱلْأَحَد	AL-AHAD	The Unique, The Only One
68	ٱلْصَّمَدُ	AS-SAMAD	The Eternal, Satisfier of Needs
69	ٱلْقَادِرُ	AL-QADIR	The Capable, The Powerful
70	ٱلْمُقْتَدِرُ	AL-MUQTADIR	The Omnipotent
71	ٱلْمُقَدِّمُ	AL-MUQADDIM	The Expediter, The Promoter
72	ٱلْمُؤَخِّرُ	AL-MU'AKHKHIR	The Delayer, the Retarder
73	ٱلْأَوَّلُ	AL-AWWAL	The First
74	ٱلْآخِرُ	AL-AAKHIR	The Last
75	ٱلْظَّاهِرُ	AZ-DHAAHIR	The Manifest
76	ٱلْبَاطِنُ	AL-BAATIN	The Hidden One, Knower of the Hidden

77	ٱلْوَالِي	AL-WAALI	The Governor, The Patron
78	ٱلْمُتَعَالِي	AL-MUTA’ALI	The Self Exalted
79	ٱلْبَرُّ	AL-BARR	The Source of Goodness, the Kind Benefactor
80	ٱلتَّوَّابُ	AT-TAWWAB	The Ever-Pardoning, The Relenting
81	ٱلْمُنْتَقِمُ	AL-MUNTAQIM	The Avenger
82	ٱلْعَفُوُّ	AL-‘AFUWW	The Pardoner
83	ٱلرَّؤُفُ	AR-RA’OOF	The Most Kind
84	مَالِكُ ٱلْمُلْكُ	MAALIK-UL-MULK	Master of the Kingdom, Owner of the Dominion
85	ذُو ٱلْجَلَالِ وَٱلْإِكْرَامُ	DHUL-JALAALI WAL-IKRAAM	Possessor of Glory and Honour, Lord of Majesty and Generosity
86	ٱلْمُقْسِطُ	AL-MUQSIT	The Equitable, the Requiter
87	ٱلْجَامِعُ	AL-JAAMI’	The Gatherer, the Uniter
88	ٱلْغَنِيُّ	AL-GHANIYY	The Self-Sufficient, The Wealthy
89	ٱلْمُغْنِيُّ	AL-MUGHNI	The Enricher
90	ٱلْمَانِعُ	AL-MANI’	The Withholder
91	ٱلضَّارُ	AD-DHARR	The Distresser
92	ٱلنَّافِعُ	AN-NAFI’	The Propitious, the Benefactor
93	ٱلنُّورُ	AN-NUR	The Light, The Illuminator
94	ٱلْهَادِي	AL-HAADI	The Guide
95	ٱلْبَدِيعُ	AL-BADEE’	The Incomparable Originator
96	ٱلْبَاقِي	AL-BAAQI	The Ever-Surviving, The Everlasting
97	ٱلْوَارِثُ	AL-WAARITH	The Inheritor, The Heir

98	ٱلرَّشِيدُ	AR-RASHEED	The Guide, Infallible Teacher
99	ٱلصَّبُورُ	AS-SABOOR	The Forbearing, The Patient

በዐማርኛ ደግሞ ይህንን ራሱን እንመልከተው፥

1) አላህ፦ የሁለንተናዊ አምላካዊ ባህሪያት ባለቤት የሆነን አካል የሚያመለክት ስም ነው።
2) አል - ረሕማን፦ ሙእሚንም ካሐዲም ለሆኑ ፍጡራን እዝነቱ ሰፊና ትልቅ ፡ ፡
3) አር - ረሒም፦ ከስራ እጥፍ ድርብ የላቀ ምንዳ የሚሰጥ (ለሙእሚኖች በተለየ ሁኔታ በጎ ዋይ እና አዛኝ) ፡ ፡
4) አል - መሊክ፦ በግዛቱ ያሻውን የሚፈጽም ንጉስ ፡ ፡
5) አል - ቁዱስ፦ በስሜት ሕዋሳት ሊደረስበት ወይም በምናብ ሊታሰብ ከሚችል ባህሪ ሁሉ የጸዳ ፡ ፡
6) አስ - ሰላም፦ ከነውር እና ከጉድለት የጸዳ፤ ሰላሙን በፍጡራኑ ላይ የሚያሰፍን ፡ ፡
7) አል - ሙእሚን፦ ራሱ፣ መጽሐፍቱና መልእክተኞቹ ስለርሱ የተናገሩትን የሚያጸድቅ ፡ ፡
8) አል - ሙሀይሚን፦ በምሉእ ችሎታው ሁሉንም ነገር የሚቆጣጠር ፡ ፡
9) አል - ዓዚዝ፦ አቻ የለሽ ሐያልና አሸናፊ ፡ ፡
10) አል - ጀባር፦ ፈቃዱን በሐይል የሚፈጽም፣ ጠጋኝ እና ፈዋሽ ፡ ፡
11) አል - ሙተከቢር፦ የልዕልና ባህሪያቱ ብቸኛ ባለቤት፣ ከጉድለትና አንዳች ነገር ከመከጀል የጸዳ ፡ ፡
12) አል - ኻሊቅ፦ ፍጡራንን በፈቃዱ ያስገኘ ፡ ፡
13) አል - ባሪእ፦ ለፍጡሮቹ የተለያዩ ገጽታዎችን በማላበስ አንዱ ከሌላው እንዲለይ ያደረገ ጠቢብ ፡ ፡
14) አል - ሙሶዊር ፡ - ለእያንዳንዱ ፍጡር የተለየ ቅርጽ የሰጠ ፡ ፡
15) አል - ገፋር፦ መጥፎ ድረጊትን በዱንያ (በምድራዊ ሕይወት) የሚሸፍን፣ በመጭው ዓለም ደግሞ ይቅር የሚል ፡ ፡
16) አል - ቀህሃር፦ አምባገኖችን ሁሉ የሚያሸንፍ ፡ ፡
17) አል - ወህሃብ፦ በችሮታው የሚያንበሸብሽ ፡ ፡
18) አል - ረዛቅ፦ ሲሳዮችን የፈጠረና ወደ ፍጡራኑ የሚያደርስ ፡ ፡
19) አል - ፈትታሕ፦ ለባሮቹ የችሮታውን ካዝናዎች የሚከፍት ፡ ፡
20) አል - ዓሊም ፡ - በእውቀቱ ሁሉንም ነገር ያካበበ ፡ ፡
21) አል - ቃቢድ ፡ - ከፍጡራኑ ለሚሻው፣ የፈለገውን ነገር የሚነሳ ፡ ፡
22) አል - ባሲጥ ፡ - ምስጢራቱን ለሚሻው አካል የሚያካፍል
23) አል - ኻፊድ ፡ - ካሐድያንና ወንጀለኞችን ዝቅ የሚያደርግ
24) አር - ራፊዕ ፡ - ወዳጆቹን ከፍ የሚያደርግ
25) አል - ሙዒዝ ፡ - እርሱን ለሚታዘዙ አማኞች ክብር የሚለግስ
26) አል - ሙዚል ፡ - ከሀዲያንን የሚያዋርድ
27) አስ - ሰሚዕ ፡ - ድምጾች የማያመልጡት
28) አል - በሲር ፡ - ፍጡራንን ሁሉ የሚመለከት
29) አል - ሐኪም ፡ - የነገሮችና የፍርዶች ሁሉ መመለሻ
30) አል - ዓድል ፡ - በግዛቱ ውስጥ ነውር ወይም ጉድለት የሌለበት
31) አል - ለጢፍ ፡ - ለባሮቹ የሚያዝን
32) አል - ኸቢር ፡ - ግልጽም ስውርም የሆኑ ነገሮችን ሁሉ የሚያውቅ
33) አል - ሐሊም ፡ - ለቅጣት የማይቸኩል
34) አል - ዐዚም ፡ - ከአእምሮ ግንዛቤና ችሎታ በላይ የሆነ
35) አል - ገፉር ፡ - ጠላቱን የሚምርና ተውበትን የሚቀበል
36) አሽ - ሸኩር ፡ - ባሮቹን የሚመነዳ
37) አል - ዐሊይ ፡ - ከሁሉ በላይ የኾነው
38) አል - ከቢር ፡ - ከአልባሌ ነገሮች የጠራ
39) አል - ሐፊዝ ፡ - ፍጡራንን ከመናጋት የሚጠብቅ
40) አል - ሙቂት ፡ - ለፍጡራን ቀለባቸውን የሚፈጥር እና የሚያከፋፍል

41) አል-ሐሲብ፡- የፍጡራንን ጉዳይ ያለ ተጋሪ የሚያከናውን፣ ለጉዳያቸው በቂ
42) አል-ጀሊል፡- ልእልናውና ምሉእነቱ የላቀ
43) አል-ከሪም ፡- ስጦታው የማይነጥፍ
44) አር-ረቂብ፡- ፍጡራንን የሚያውቅና የሚከተታተል
45) አል-ሙጂብ፡- ዱዓን ተቀባይ
46) አል-ዋሲዕ ፡- ዙፋኑ ከሰማያትና ከምድር የሰፋ
47) አል-ሐኪም፡- ከምሉእነቱና ከልቅናው ጋር የሚቃረኑ ተግባራትን ከመፈጸም የጠራ
48) አል-ወዱድ፡- በፍጡራኑ ዘንድ የሚወደድ
49) አል-መጂድ፡- በማንነቱም ሆነ በስራው የላቀ፣ ችሮታውም ብዙ።
50) አል-ባኢሥ፡- ሙታንን ለምርመራ የሚቀሰቅስ
51) አሽ-ሸሂድ ፡- ግልጽም ስውርም የሆኑ ጉዳዮችን ሁሉ የሚመለከት
52) አል-ሐቅ፡- ሁሉንም ነገር በጥበብ የፈጠረ
53) አል-ወኪል፡- የሁሉንም ጉዳዮች ሐላፊና ከዋኝ።
54) አል-ቀዊይ፡- ምንም ነገር የማይሳነው
55) አል-መቲን፡- ምንም ነገር የማያሸንፈው
56) አል-ወሊይ፡- በወዳጆቹ ተወዳጅ፣ የነርሱ ረዳትና አለኝታ
57) አል-ሐሚድ፡- ለምስጋናና ለውዳሴ ተገቢ
58) አል-ሙሕሲ፡- ጥቃቅን ጉዳዮች የማያመልጡትና ታላላቆች የማይሳኑት
59) አል-ሙብዲእ፡- ፍጡራንን መጀመሪያ ካልነበሩበት ያስገኘ ፈጣሪ
60) አል-ሙዒድ፡- ፍጡራንን ወደ ሞት የሚመልስ (መላሽ)
61) አል-ሙሕይ፡- የበሰበሱ አጥንቶችን ዳግመኛ ሕያው የሚያደርግ
62) አል-ሙሚት፡- ነፍስን ከአካል በመነጠል የሚገድል
63) አል-ሐይ፡- ዘልዓለማዊ ሕይወት ያለው (ሕያው)
64) አል-ቀዩም፡- ሁሉንም ነገር ያለ ረዳት የሚያከናውን (ራሱን ቻይ)
65) አል-ዋጂድ፡- የሚፈልገውንና ያሻውን ሁሉ ማግኘት የሚችል (አግኝ)
66) አል-ማጅድ፡- የተላቀ ችሮታና በጎ ምግባር ባለቤት
67) አል-ዋሒድ፡- በማንነቱም፣ በባህሪውም፣ በስራውም መሰል የለሽ (ብቸኛ)
68) አስ-ሰመድ፡- ጉዳዮች የሚከጀሉበት (መጠጊያ)
69) አል-ቃዲር፡- ፍጡራኑን በመፍጠር ብቸኛ የሆነ
70) አል- ሙቅተዲር፡- የሻውን ነገር የሚወስን
71) አል-ሙቀዲም፡- ነብያትን፣ ወዳጆቹንና ከፍጡራን የሚሻውን የሚያስቀድም
72) አል-ሙኣኺር፡- ጠላቶቹን (ከእዝነቱ) በማራቅ የሚያዘገይ
73) አል-አወል፡- ሁሉንም ነገር የቀደመ
74) አል-አኺር፡- ፍጡራን ከጠፉ በኋላ ወደኋላ የሚቀር
75) አዝ-ዛሂር፡- በምልክቶቹ፣ በተአምራቱና በአድራጉቱ ሕልውናው ግልጽ የሆነ
76) አል-ባጢን፡- ከእይታ የተሰወረ፣ ሚስጥራትን ሁሉ አዋቂ
77) አል-ዋሊ፡- የነገሮች ባለቤት፣ በችሮታው ውለታ የሚውል፣ መከራን የሚከላከል።
78) አል-ሙተዓል፡- ደረጃው ከፍ ያለ፣ የዐርሽ ባለቤት፣ በክብሩና በሕልውናው የላቀ
79) አል-በር፡- ለለመኑት ቸር
80) አት-ተዋብ፡- ከባሮቹ ተውበትን ንስሃን የሚቀበልና ሐጢአትን ይቅር የሚል
81) አል-ሙንተቂም፡- ብቀላው የሚፈራ፣ እዝነቱ በፍርሃትና በተስፋ የሚከጀል
82) አል-ዓፍዉ፡- ወንጀልን የሚያብስ፣ ጥፋትንና ወንጀልን የሚያልፍ
83) አር-ረኡፉ ፡- ለባሮቹ በጣም አዛኝ
84) ማሊከል ሙልክ፡- ፍላጎቱን ያለገደብ ፈጻሚ፣ በንግስናው የፈለገውን በፈለገው ቦታና በፈለገው ጊዜ የሚያደርግ፣ ውሳኔው የማይሻር በፈረደው የማይቀጣ
85) ዙልጀላሊ ወልኢክራም፡- የልእልናዎችና የልቅናዎች ሁሉ ባለቤት፣ ከፍጡራኑም የላቀ።
86) አል-ሙቅሲጥ፡- ፍትሕ አስፋኝ (ፍትሐዊ)
87) አል-ጃሚዕ፡- በማንነቱ፣ በባህሪውና በስራው ምሉእ ባህሪያትን ሁሉ የሰበሰበ (ሰብሳቢ)
88) አል-ገንይ፡- በማንነቱ፣ በሕልውናውም ሆነ በስራው አንዳች ነገር የማይከጅል (ሐብታም)

89) አል-ሙሚኒ፡- ከባሮቹ ለሚሻው ሰው የሚሰጥ
90) አል-ሚኒዕ፡- ባሮቹን ለመጠበቅ መከራን የሚያስቀርና ለፈተና ችሮታውን የሚያቅብ
91) አድ-ዲር፡- ከባሮቹ የሚሻውን የሚጎዳ፣ የጉዳት ባለቤት
92) አን-ናፊዕ፡- የመጥቀም ባለቤት፣ በሁሉም ነገር ላይ ቻይ
93) አን-ኑር፡- በተውሒዱ የእውነተኞችን ልቦናዎች የሚያበራ
94) አል-ሃዲ፡- ሁሉንም ነገር የፈጠረና የመራ
95) አል-በዲዕ፡- ጥበበ-ረቂቅ ፈጣሪ
96) አል-ባቂ፡- ዝንተ ዓለም የሚኖር
97) አል-ዋሪስ፡- በሰማያትና በምድር ያሉ ፍጡራን ሁሉ ባለቤት፣ የሁሉም ነገር ጌታ፣ ሲሳይ ለጋሽና አዛኝ
98) አር-ረሺድ፡- እርሱን ለሚታዘዙና ለሚገዙ ሰዎች ቅኑን ጎዳና አመላካች
99) አስ-ሰቡር፡- ጊዜ የሚሰጥ፣ የሚታገስ፣ የማይቸኩል።

ሁለቱ ጽሑፎች ጥቂት ልዩነት ያላቸው ቢሆንም ቢያንስ ዋነኛ ሐሳቡን ለማስተላለፍ በቂ ናቸው። ስለዚህ እነዚህን ስሞች በሙሉ ከተረዳን የጌታችንን አምላክነት በግልጥ ማሳየት እንችላለን።

1) የአላህ ስሞች ውስጥ ለጌታችን የተሰጡ ስሞችን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እናገኛለን።

ሀ) አላህ 'አል-አወል' (የመጀመሪያ) ነው 'አል-አኺር' (የመጨረሻ) ነው

አላህ ከስሞቹ መካከል ባሕርዩን የሚገልጡ ሁለት ስሞች 'አል-አወል' (የመጀመሪያ) እና 'አል-አኺር' (የመጨረሻ) ናቸው። ይህ ማለት ከዓለም መገኘት በፊት፣ ከጊዜ በፊት፣ ከሁሉ ነገር በፊት የነበረ ከዚያም ደግሞ ዓለምም ካለፈ በኋላ የሚኖር፣ ከጊዜ በኋላም ደግሞ የሚኖር ማለት ነው። በቀላል ዐማርኛ አላህ ዘለዓለማዊ ነው ማለት ነው። ይህንን ቃል ማንም ቢሆን ከአላህ በቀር ሊጠቀም አይችልም። ይህንን በቁርአን ውስጥ በግልጥ እንመለከተዋለን፥

/ሱራ 57 ፥ 3/ (ሱረቱ አል-ሐዲድ ኣያ 3)

https://quranenc.com/am/browse/amharic_sadiq/57/#3

"እርሱ ፊትም ያለ፣ ኋላም ቀሪ፣ ግልጽም፣ ስውርም ነው። እርሱም ነገሩን ሁሉ ዐዋቂ ነው።"

{ከአላህ በቀር ማንም ቢሆን ፊትም ያለ ተብሎ አይጠራም ፥ ከአላህ በቀር ማንም ቢሆን ኋላም ቀሪ ተብሎ ሊጠራ አይችልም። ቁርአን ይህንን በግልጥ ያስቀምጣል ፥ ከዚያም ደግሞ ብሉይ ኪዳንም አምላክ ብቻውን 'አል-አወል'ና 'አል-አኺር' እንደሆነም ይነግረናል።

/ኢሳ 44 ፥ 6/

"6 የእስራኤል ንጉሥ እግዚአብሔር፥ የሚቤዠውም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እኔ ፊተኛ ነኝ እኔም ኋለኛ ነኝ፥ ከእኔ ሌላም አምላክ የለም።"

ስለዚህ አምላካችን በብሉይ ኪዳንም ቢሆንም ብቻውን ፊተኛና ኋላኛ ነው ፥ ደግሞ የሚደንቀው ሐዲስ ኪዳንም ያንኑ ራሱን ትምህርት ያስተምራል።

/ራእ 1 ፥ 17/

“17 ባየሁትም ጊዜ እንደ ሞተ ሰው ሆኜ ከእግሩ በታች ወደቅሁ። ቀኝ እጁንም ጫነብኝ እንዲህም አለኝ፦ አትፍራ፤ ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ፥”

ሐዲስ ኪዳንም ይስማማል ምክንያቱም ቅዱስ ዮሐንስ በፊቱ የወደቀለት አካል ‘አምላክ’ ብቻ ነው ሊሆን የሚችለው አይደል? ‘አላህ’ ነው ሊሆን የሚችለው አይደል? ከአላህ ውጪ ማንም ሊሆን አይችልም አይደል? ከአላህ ውጪ ማንም ‘ፊተኛውና ኋለኛው ነኝ’ ሊል አይችልም አይደል? ‘አምን’ እሺ እንቀጥል።

/ራእ 1 ፥ 17 - 18/

“17 ባየሁትም ጊዜ እንደ ሞተ ሰው ሆኜ ከእግሩ በታች ወደቅሁ። ቀኝ እጁንም ጫነብኝ እንዲህም አለኝ፦ አትፍራ፤ ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ፥

18 ሞቼም ነበርሁ እነሆም፥ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ፥ የሞትና የሲኦልም መክፈቻ አለኝ።”

[መቼ ነው አላህ የሞተው? ከዚያ ደግሞ መቼ ነው አላህ ሞቶ የተነሣው???

እስኪ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሞቶ ድጋሚ ላይሞት የተነሣው ማን ነው? ጌታችን አምላካችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ እና ብቻ ነው። ስለዚህ እንደቁጥር 17 የሞተውና የተነሣው ራሱ የክብር ባለቤት ክርስቶስ አላህ ነው ማለት ነው። ስለዚህ ጌታችን ራሱ አምላክ ነው ማለት ነው።]}

ለ) አል-ሐቅ (እውነት)

/ሱራ 22 ፥ 62/ (ሱረቱ አል-ሐጅ ኣያ 62)

https://quranenc.com/am/browse/amharic_sadiq/22/#62

“ይህ አላህ እርሱ እውነት በመሆኑ ከእርሱም ሌላ የሚግገዙት ነገር እርሱ ፍጹም ውሸት በመሆኑ አላህም እርሱ የሁሉ በላይ ታላቅ በመኾኑ ነው።”

/ዮሐ 14 ፥ 6/

“6 ኢየሱስም፦ እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።”

ሙስሊሞች እንዲሁ እውነት ነው ያለው እንጂ ‘አል-ሐቅ’ (The Truth) አላለም እንዳይሉ። በዐረብኛ፣ በግሪክና በኢንግሊዘኛ አመጣዋለሁኝ። ከዚያ በኋላ ሙስሊሞች ይህንን መካድ አይችሉም።

/ዮሐ 14 ፥ 6/

በዐረብኛ ፥ "6 قال له يسوع انا هو الطريق **والحق** والحياة. ليس احد يأتي الى الآب الا بي."

በግሪክ ፥
"6 λέγει αὐτῷ [ὁ] Ἰησοῦς, Ἐγώ εἰμι ἡ ὁδὸς καὶ **ἡ ἀλήθεια** καὶ ἡ ζωή· οὐδεὶς ἔρχεται πρὸς τὸν πατέρα εἰ μὴ δι' ἐμοῦ." (https://www.greekbible.com/john/14/6)

በኢንግሊዘኛ ፥ "Jesus said to him, "I am the way, **the truth**, and the life. No one comes to the Father except through Me." (https://www.biblegateway.com/passage/?search=john+14%3A6&version=NKJV)

ሐ) አል-ሙሕይ (ሕያው የሚያደርገው)

/ሱራ 22 ፥ 62/ (ሱረቱ አል-ሐጅ ኣያ 62)

https://quranenc.com/am/browse/amharic_sadiq/22/#62

"ይህ አላህ እርሱ እውነት በመሆኑ ከእርሱም ሌላ የሚግገዙት ነገር እርሱ ፍጹም ውሸት በመሆኑ አላህም እርሱ የሁሉ በላይ ታላቅ በመኾኑ ነው።"

/ዮሐ 3 ፥ 16/

"16 በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።"

/ዮሐ 3 ፥ 36/

"36 በልጁ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፤ በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቍጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም።"

/ዮሐ 6 ፥ 40/

"40 ልጁንም አይቶ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወትን እንዲያገኝ የአባቴ ፈቃድ ይህ ነው፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ።"

/ዮሐ 6 ፥ 44/

"44 የላከኝ አብ ከሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ።"

/ዮሐ 6 ፥ 54/

“54 ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ።”

መ) አላህ

አላህ በተደጋጋሚ ለእስላሙ አምላክ የተሰጠ ስም ነው። ይህ ስም ግን በቀላሉ ‘አል-ኢለሕ’ ማለት ነው። ክርስቲያኖችም በዐረብኛ ሲናገሩ እኒህን ቃላት ይጠቀማሉ። እንደዚያ ይጠቀማሉ ማለት ግን የክርስቲያኖች አምላክና የሙስሊሞች አምላክ አንድ ነው ማለት አይደለም። የሙስሊሞች አምላክ ሰይጣን ነው። ለዚያ ነው እግዚአብሔር ይመልሳቸው የምንለው። ለምኑም ‘ኢለህ’ የሚል ስም ስትመለከቱ ‘አምላክ’ ማለት ነው ፥ ‘አላህ’ ማለት ግን ‘አል-ኢለህ’ ማለት ነው። በሌላ አነጋገር ለሌላ አምላክ የማይሰጥ ልዩ ስም ማለት ነው። በሌላ አነጋገር እኛ ‘እግዚአብሔር’ እንደምንለው ማለት ነው። ሌሎችን ‘አማልክት’ ልንል እንችላለን ፥ ነገር ግን ‘እግዚአብሔር’ አንላቸውም። እንደዚሁ ሁሉ ለሌሎች የውሸት አማልክት ‘ኢለህ’ ሲባል ይችላል ፥ ግን መቼም ቢሆን ከእግዚአብሔር በቀር ‘አላህ’ ተብሎ የሚጠራ የለም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ‘አላህ’ ተብሎ ሲጠራ እናሳያለን።

/ዕብ 1 ፥ 8 – 12/

“8 ስለ ልጁ ግን፦ አምላክ ሆይ፥ ዙፋንህ እስከ ዘላለም ድረስ ይኖራል፤ የመንግሥትህ በትር የቅንነት በትር ነው።

9 ጽድቅን ወደድህ ዓመፅንም ጠላህ፤ ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክህ ከጓደኞችህ ይልቅ በደስታ ዘይት ቀባህ ይላል።

10 ደግሞ፦ ጌታ ሆይ፥ አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ፥ ሰማዮችም የእጆችህ ሥራ ናቸው፤

11 እነርሱም ይጠፋሉ አንተ ግን ጸንተህ ትኖራለህ፤ ሁሉም እንደ ልብስ ያረጃሉ፥

12 እንደ መጎናጸፊያም ትጠቀልላቸዋለህ ይለወጡማል፤ አንተ ግን አንተ ነህ፥ ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም ይላል።”

ይህንን በዐረብኛ ብናገኘው እንዲህ ብሎ ይነበባል።

/ዕብ 1 ፥ 8 – 12/

“8 احببت البر وابغضت الاثم من اجل ذلك 9 . واما عن الابن كرسيك **يا الله** الى دهر الدهور. قضيب استقامة قضيب ملكك 10 . مسحك الله الهك بزيت الابتهاج اكثر من شركائك 11 . وانت يا رب في البدء اسست الارض والسموات هي عمل يديك 12 هي تبيد وكرداء تطويها فتتغيّر ولكن انت انت وسنوك لن تفنى ولكن انت تبقى وكلها كثوب تبلى .”

{በዐረብኛው ውስጥ ዕብ 1 ፥ 8 የሚነበበው እንዲህ ብሎ ነው ፥ “ወመ አንኢል ኢብን ኩርሲዩክ **ያ አላህ** ዳህር አልዱሁር” ብሎ አብ ለልጁ ለወልድ ለኢየሱስ ክርስቶስ ‘ያ አላህ’ ብሎ ጠራው። መቼም ‘አላህ’ ለፍጡር ይሰጣል አትሉኝብ ብዬ ተስፋ አድርጋለሁኝ ፥ አይደል ሙስሊሞች። በግልጥ ጌታችን በዚህ ጥቅስ ውስጥ አምላክ ተብሎ ተጠርቷል።}

2) በመጨረሻው ዓለምን ሁሉ ለመዳኘትና ለመፍረድ የሚመጣው እርሱ ነው

/ሱራ 1 ፥ 4/ (ሱረቱ አል-ፋቲሃ ኣያ 4)

https://quranenc.com/am/browse/amharic_sadiq/1/#4

“የፍርዱ ቀን ባለቤት ለኾነው።“

{አላህ ‘መሊክ የውሚል ዲን’ ወይም ‘የፍርዱ ቀን ባለቤት’ እየተባለ ይጠራል። በመጨረሻው የፍርድ ቀን ሁሉንም የሚፈርድባቸው አምላክ እንደሆነ በቁርአን ውስጥ ይነገርለታል። አሁን ደግሞ እስኪ ራሱን ቃል ደግሞ ለጌታችን ሐዲስ ኪዳን ሲናገረው እንመልከታለን።}

/ማቴ 25 ፥ 31 – 46/

“31 የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱም ጋር ቅዱሳን መላእክቱ ሁሉ፥ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣልና፤

32 አሕዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፤ እረኛም በጎቹን ከፍየሎች እንደሚለይ እርስ በርሳቸው ይለያቸዋል፥

33 በጎችን በቀኙ ፍየሎችንም በግራው ያቆማቸዋል።

34 ንጉሡም በቀኙ ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል፦ እናንተ የአባቴ ቡሩካን፥ ኑ፤ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ።

35 ተርቤ አብልታችሁኛልና፥ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፥ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና፥ ታርዤ አልብሳችሁኛልና፥

36 ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፥ ታስሬ ወደ እኔ መጥታችኋልና።

37 ጻድቃንም መልሰው ይሉታል፦ ጌታ ሆይ፥ ተርበህ አይተን መቼ አበላንህስ? ወይስ ተጠምተህ አይተን መቼ አጠጣንህ?

38 እንግዳ ሆነህስ አይተን መቼ ተቀበልንህ? ወይስ ታርዘህ አይተን መቼ አለበስንህ?

39 ወይስ ታመህ ወይስ ታስረህ አይተን መቼ ወደ አንተ መጣን?

40 ንጉሡም መልሶ፦ እውነት እላችኋለሁ፥ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት ይላቸዋል።

41 በዚያን ጊዜ በግራው ያሉትን ደግሞ ይላቸዋል፦ እናንተ ርጉማን፥ ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ሂዱ።

42 ተርቤ አላበላችሁኝምና፥ ተጠምቼ አላጠጣችሁኝምና፥ እንግዳ ሆኜ አልተቀበላችሁኝምና፥

43 ታርዤ አላለበሳችሁኝምና፥ ታምሜ ታስሬም አልጠየቃችሁኝምና።

44 እነርሱ ደግሞ ይመልሱና፦ ጌታ ሆይ፥ ተርበህ ወይስ ተጠምተህ ወይስ እንግዳ ሆነህ ወይስ ታርዘህ ወይስ ታመህ ወይስ ታስረህ መቼ አይተን አላገለገልንህም? ይሉታል።

45 ያን ጊዜ፦ እውነት እላችኋለሁ፥ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ለአንዱ ስላላደረጋችሁት ለእኔ ደግሞ አላደረጋችሁትም ብሎ ይመልስላቸዋል።

46 እነዚያም ወደ ዘላለም ቅጣት፥ ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ።”

{ቁርአን በመጨረሻ ቀን የሚመጣው አላህ ነው አለን ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ ጌታችን ስለራሱ የምመጣው እኔው ራሴው ነኝ ብሎ ነገረን። በሰዎች ሁሉ ላይ የምፈርድባቸው፣ እንደየዋጋቸው የምሰጣቸው እኔ ነኝ ብሎ አስተማረን። ስለዚህ በሌላ አነጋገር እኔ የምመጣው አምላክ ነኝ ፥ የምመጣው ነኝ ብሎ ቃል በቃል ነገረን ማለት ነው። እንዲያውም በሐዲሥ ላይማ ጌታችን የሚለውን ቃል ወስዶ መሐመድ በአላህ አፍ ውስጥ ሲከተው ይገኛል። እስኪ ይህንን እንመለከተው ፥ በመጀመሪያ የጌታችንን አንብቡትና ከዚያ በሐዲሥ ውስጥ ያለውን ደግሞ ተመልከቱት፥

/Hadith Qudsi/ (https://sunnah.com/qudsi40:18)

“Allah (mighty and sublime be He) will say on the Day of Resurrection: O son of Adam, I fell ill and you visited Me not. He will say: O Lord, and how should I visit You when You are the Lord of the worlds? He will say: Did you not know that My servant So-and-so had fallen ill and you visited him not? Did you not know that had you visited him you would have found Me with him? O son of Adam, I asked you for food and you fed Me not. He will say: O Lord, and how should I feed You when You are the Lord of the worlds? He will say: Did you not know that My servant So-and-so asked you for food and you fed him not? Did you not know that had you fed him you would surely have found that (the reward for doing so) with Me? O son of Adam, I asked you to give Me to drink and you gave Me not to drink. He will say: O Lord, how should I give You to drink when You are the Lord of the worlds? He will say: My servant So-and-so asked you to give him to drink and you gave him not to drink. Had you given him to drink you would have surely found that with Me.

It was related by Muslim.”

/አላህ (ሱ.ወ) በትንሣኤ ቀን፥- የአደም ልጅ ሆይ፥- ታምሜአለሁ፥ አንተም አልጎበኘኸኝም ይላል። እርሱም፥- ጌታ ሆይ፣ አንተ የአለማት ጌታ ስትሆን እንዴት ልጎበኝህ? እርሱም ይላል፥- ባርያዬ እንደታመመና እንዳልጎበኛኸት አታውቁምን? አንተ ብትጐበኘው ከእርሱ ጋር እንደምታገኝኝ አታውቅምን? የአደም ልጅ ሆይ ምግብን ጠየቅሁህ አላበላኸኝምም። ጌታ ሆይ አንተ የዓለማት ጌታ ስትሆን እንዴት ልመግብህ? እርሱም ይላል፥- «ባሪያዬ ምግብ እንደጠየቀህ አላመገበህምን? እሱን ብትመግበው ኖሮ እኔ ዘንድ ያንን (ይህን የሠራህበትን ዋጋ) በእርግጥ እንደምታገኘው አታውቅምን? የአደም ልጅ ሆይ ታጠጣኝ ዘንድ ጠየቅሁህ አላጠጣኸኝምም። እርሱም፥- አቤቱ አንተ የዓለማት ጌታ ስትሆን እንዴት አጠጣሃለሁ? እርሱም፥- ባሪያዬ ታጠጣው ዘንድ ጠየቀህ አንተም አላጠጣኸውም። ብታጠጣው ኖሮ እኔ ዘንድ በእርግጥ ባገኘኸው ነበር።

በሙስሊም የተሰበሰበ ነው።/

[ቆይ ቆይ ቆይ!!! የት ነበር ይህንን ቃል አንብቤው የማውቀው? ‘አዎን’ ከ600 ዓመት በፊት በወንጌላቱ ውስጥ ነበር ያነበብሁት። መሐመድ የጌታችንን ቃል ወስዶ አላህን ታላቅና ርኅሩኅ ለማስመሰል በሞከረበት በዚሁ ሳያውቀው የጌታችንን አምላክነት አረጋገጠ። ራስን በራስ መቅበር ይሏችኋል ፥ በራስ እግር ላይ መተኩስ ይሏችኋል ይህ ነው።] }

አስጀምሮ ላስፈጸመ ለልዑል እግዚአብሔር ክብር እና ምሥጋና ይኹን። ክርስቶስ ተነሥቷል በእውነት ተነሥቷል

ኪርያላይሶን እግዚአብሔር አብ ሆይ ማረን ፥ ኪርያላይሶን እግዚአብሔር ወልድ ሆይ ማረን ፥ ኪርያላይሶን እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሆይ ማረን። ማራናታ ፥ ጌታ ሆይ አትዘግይ ቶሎ ና።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል ወለመስቀሉ ክቡር ለዓለመ ዓለም አሜን